ደቀ መዝሙር

“ደቀ መዝሙር” ማለት ተማሪ ወይም ተከታይ ማለት ነው። ደቀ መዝሙር የሚማረው ለማወቅ ብቻ ሳ ይሆን ያወቀውን በተግባር ለማዋል ነው። በየዘመኑ ይኖሩ የነበሩ ታላላቅ አስተማሪዎች ደቀ መዛሙርት ነበሩዋቸው። ለምሳሌ፦ ኢያሱ የሙሴ ደቀ መዝሙር ነበረ። የግሪኩች ፈላስፋ ፕሌቶ የሶክራጥስ፤ አሪስ ቶትል ደግሞ የፕሌቶ ደቀ መዛሙርት እንደ ነበሩ ከታሪክ እንረዳለን

ጌታ የጠራን ለምንድነው (እርሱን ያገኘ ሰው ምን ያድርግ)?????

**የዮሐንስ ወንጌል 1:35 -41**

የመጀመሪያዎቹ የክርስቶስ ተከታዮች ውስጥ
የመጥምቁ ዮሐንስ ደቀ መዛሙርት እንደ ነበሩትና ከደቀ መዛሙርቱ አንዳንዶቹ የጌታ ደቀ መዛሙርት እ ንደ ሆኑ እንገነዘባለን።

የመጀመሪያዎቹን ተከታይ ጌታ የጥራበት ወቅት ነው .. ``````````````````````` ተከተሉኝ

ተከተሉኝ ተከተሉኝ ተከተሉኝ



ሀ/ እንድንከተለው

ለ/ ደቀ መዝሙሩ እንድንሆን

ማት 4፡20 እርሱም "ኑ ተከተሉኝ፤ ሰዎችን አጥማጆች አደርጋችኋለሁ" አላቸው። ወዲያውኑ መረባቸውን ጥለው ተከተሉት

ሉቃስ 5፡ 28

ከዚህም ቦሃላ ወጥቶ ለዊ የሚባል ቀራጭ በመቅረጫው ተቀምጦ ተመለከተዉና ተከተለኝ አለው ሁሉንም ተወ ተነስቶም ተከተለው በበቱም ታላቅ ግብዣ አደረገለት;

የማቴዎስ ወንጌል ___ 19፡ 16_29 የሀብታሙ ጥያቄ ማር 10፥17-30፤ ሉቃ 18፥18-30

16ከዚያም አንድ ሰው ወደ ኢየሱስ ቀርቦ፣ "መምህር ሆይ፤ የዘላለምን ሕይወት አገኝ ዘንድ ምን መልካ ም ነገር ልሥራ" ሲል ጠየቀው።

17ኢየሱስም፣ "ስለ መልካም ነገር ለምን ትጠይቀኛለህ? መልካም የሆነ አንዱ ብቻ ነው፤ ወደ ሕይወት ለመግባት ከፈለግህ ግን ትእዛዞቹን ጠብቅ" አለው።

18ሰውየውም፣ "የትኞቹን ትእዛዞች?" ሲል ጠየቀ።

ኢየሱስም እንዲህ አለው፤ "አትግደል፣ አታመንዝር፤ አትስረቅ፤ በሐሰት አትመስክር፤ 19አባትህንና እናት ህን አክብር፤ ጎረቤትህን እንደ ራስህ ውደድ።"

20ጕልማሳውም ሰው፣ "እነዚህንማ ጠብቄአለሁ፤ ከዚህ ሌላ የሚጐድለኝ ምን አለ?" አለው።

21ኢየሱስም፣ "ፍጹም ለመሆን ከፈለግህ፣ ሄደህ ንብረትህን ሁሉ ሽጠህ፣ ገንዘቡን ለድኾች ስጥ፤ በሰማ ይም ሀብት ታገኛለህ። ከዚያም መጥተህ ተከተለኝ" አለው።

22ጕልማሳው ሰውየም ይህን ሲሰማ፣ ብዙ ሀብት ስለ ነበረው እያዘነ ሄደ።

23ኢየሱስም ደቀ መዛሙርቱን እንዲህ አለ፤ "እውነት እላችኋለሁ፣ ለሀብታም ወደ መንግሥተ ሰማይ መግባት እጅግ አስቸጋሪ ነው። 24ደግሜ እላችኋለሁ፤ ሀብታም ወደ እግዚአብሔር መንግሥት ከሚገባ ግመል በመርፌ ቀዳዳ ቢሾልክ ይቀልላል።"

25ይህን ሲሰሙ፣ ደቀ መዛሙርቱ እጅግ በመገረም፣ "እንግዲያስ ማን ሊድን ይችላል?" ሲሉ ጠየቁ።

26ኢየሱስም እየተመለከታቸው፣ "ይህ በሰው ዘንድ አይቻልም፤ በእግዚአብሔር ዘንድ ግን ሁሉም ነገር ይቻላል" አላቸው።

27ጴጥሮስም መልሶ፣ "እኛ ሁሉን ትተን ተከትለንሃል፤ ታዲያ ምን እናገኝ ይሆን?" አለው።

28ኢየሱስም እንዲህ አላቸው፤ "እውነት እላችኋለሁ፤ በሚመጣው አዲስ ዓለም የሰው ልጅ በክብሩ ዙ
ፋን ላይ በሚቀመጥበት ጊዜ፣ እናንተም የተከተላችሁኝ በዐሥራ ሁለት ዙፋን ላይ ተቀምጣችሁ፣ በዐሥራ
ሁለቱ የእስራኤል ነገድ ላይ ትፈርዳላችሁ። 29ስለ ስሜ ብሎ ቤቶችን፣ ወንድሞችን፣ እኅቶችን፣ አባትን
፣ እናትን፣ ልጆችን ወይም ዕርሻን የሚተው ሁሉ መቶ ዕጥፍ ይቀበላል፤ የዘላለምንም ሕይወት ይወርሳል

የዮሐንስ ወንጌል 12፡25፤

ነፍሱን የሚወድ ያጠፋታል፥ ነፍሱንም በዚህ ዓለም የሚጠላ ለዘላለም ሕይወት ይጠብቃታል።

የማቴዎስ ወንጌል 10 :37፤---39

ከእኔ ይልቅ አባቱን ወይም እናቱን የሚወድ ለእኔ ሊሆን አይገባውም፤ ከእኔ ይልቅም ወንድ ልጁን ወይም ሴት ልጁን የሚወድ ለእኔ ሊሆን አይገባውም፤ መስቀሉንም የማይዝ በኋላዬም የማይከተለኝ ለእኔ ሊሆን አይገባውም  ነፍሱን የሚያገኝ ያጠፋታል፥ ነፍሱንም ስለ እኔ የሚያጠፋ ያገኛታል።

የሉቃስ ወንጌል 14:26 27

ማንም ወደ እኔ የሚመጣ ቢኖር አባቱንና እናቱን ሚስቱንም ልጆቹንም ወንድሞቹንም እኅቶቹንም የራሱን ሕይወት ስንኳ ሳይቀር ባይጠላ፥ ደቀ መዝሙሬ ሊሆን አይችልም።
ማንም መስቀሉን ተሸክሞ በኋላዬ የማይመጣ፥ ደቀ መዝሙሬ ሊሆን አይችልም።

የሉቃስ ወንጌል 9:23—24

- ለሁሉም እንዲህ አላቸው፡- በኋላዬ ሊመጣ የሚወድ ቢኖር፥ ራሱን ይካድ መስቀሉንም ዕለት ዕለት ተሸክሞ ይከተለኝ።

፤ ነፍሱን ሊያድን የሚወድ ሁሉ ያጠፋታልና፤ ስለ እኔ ነፍሱን የሚያጠፋ ሁሉ ግን እርሱ ያድናታል

የማቴዎስ ወንጌል 19:29፤

ስለ ስሜም ቤቶችን ወይም ወንድሞችን ወይም እኅቶችን ወይም አባትን ወይም እናትን ወይም ሚስትን ወይም ልጆችን ወይም እርሻን የተወ ሁሉ መቶ እጥፍ ይቀበላል የዘላለምንም ሕይወት ይወርሳል።

የማርቆስ ወንጌል 8:35፤

ነፍሱን ሊያድን የሚወድ ሁሉ ያጠፋታልና፥ ስለ እኔና ስለ ወንጌል ነፍሱን የሚያጠፋ ሁሉ ግን ያድናታል ።

የሐዋርያት ሥራ 20:24፤

ነገር ግን ሩጫዬንና ከጌታ ከኢየሱስ የተቀበልሁትን አገልግሎት እርሱም የእግዚአብሔርን ጸጋ ወንጌልን መመስከር እፈጽም ዘንድ ነፍሴን በእኔ ዘንድ እንደማትከብር እንደ ከንቱ ነገር እቆጥራለሁ።

- ❖ ደቀ መዝሙርነት ለምን አስፈለገ?
- ➢ የጌታ የኢየሱስ ትዕዛዝ ስለሆነ
  - ✓ ሂዱ _
  - ✓ አጥምቁ
  - ✓ አስተምሩ _ ያዘዝኩዋችሁን እንዲጠብቁ
  - ✓ ደቀ መዛሙርት አድርጉ

እኔ እስከዓለም ፍጻሜ ከናንተ ጋር ነኝ

የጌታ ደቀ መዛሙርት ልንሆን ነው ጥሪያችን

ኢየሱስ ዓለም አቀፍ የሆነውን የማዳን ዓላማውን ለማዳረስ ሕዝቡን ከማስተማር ሌላ አስራ አንድ ደቀ መዛሙርት አሠልጥኗል። አስራ አንዱ ደቀ መዛሙርት በመንፈስ ቅዱስ መሪነትና ረድኤት የወንጌል መል እክት ዛሬ የደረሰበት ሁኔታ ላይ አድርሰዋል።

ወንጌልን ወደ ዓለም ሁሉ የማድረስ ተግባር ዛሬም ገና አላበቃም፤ ወንጌል ያልሰሙ፣ ሰምተውም ያልገባ ቸው፣ ገብቷቸው ተገቢ ምላሽ ያልሰጡ ገና ብዙ ሰዎች አሉ። ወንጌልን ወደ ዓለም ሁሉ ለማድረስ ዋነኛ መንገድ በመንፈስ ቅዱስ መሪነትና ረድኤት ደቀ መዛሙርት ማፍራት ነው።

- ❖ ጌታ በማቴዎስ ወንጌል ምዕራፍ 28 ከቁጥር 16-20

ከሰጠው ትዕዛዝ ደቀ መዛሙርት ለማፍራት የሚረዱንን ስድስት ነጥቦች እንመለከታለን። ከእኛ ጋር መሆኑን ማወቅ ያስፈልጋል። እስቲ እነዚህን ነጥቦች በዝርዝር እንመልከታቸው፤

1. *ደቀ መዛሙርት ማፍራት የጌታ ትዕዛዝ መሆኑን መገንዘብ ያስፈልጋል።* “አስራ አንዱ ደቀ መዛሙርት ባዩትም ጊዜ ሰገዱለት፤ ኢየሱስም ቀረበና እንዲህ ብሎ ተናገራቸው፡- ሥልጣን ሁሉ በሰማይና በምድር ተሰጠኝ” (ማቴዎስ 28፡ 16-28)። ጌታ ይህን ቃል ለደቀ መዛሙርቱ የተናገረው የኃጢአታችንን ዕዳ ለመክፈል በመስቀል ላይ ተሰቅሎ ሞትን ድል አድርጐ ከተነሳ በኋላ ወደ አብ ከማረጉ በፊት ነበር። ጌታ ለደቀ መዛሙርቱ በክብሩና በታላቅነቱ ታያቸው፤ እነርሱም በአክብሮት፣ በአድናቆት፣ በአምልኮ፡- አምላካችን፣ ጌታችን አንተ ታላቅ ነህ፣ አንተ ኃያል ነህ፣ ሁሉን ቻይ ነህ ብለው ሰገዱለት። እርሱም ስግደታቸውንና አምልኰአቸውን ተቀበለ። “ሥልጣን ሁሉ በሰማይና በምድር ተሰጠኝ” ብሎ ደቀ መዛሙርት እንዲያፈሩ ትዕዛዝ ሰጣቸው። ጌታ የሰጣቸው ምክር ሳይሆን ትዕዛዝ ነው። ደቀ መዛሙርት ማፍራት ትዕዛዝ ነው። ትዕዛዙ የድርጅት ወይም የቤተ ክርስቲያን ወይም የሃይማኖት መሪዎች ትዕዛዝ አይደለም። የምድራዊ ባለሥልጣንም ትዕዛዝ አይደለም። ሥልጣን ሁሉ በሰማይና በምድር የእርሱ የሆነ የጌታ ኢየሱስ ትዕዛዝ ነው።

የምድራዊ ባለሥልጣንን ትዕዛዝ የምናከብር ከሆነ፣ ሥልጣን ሁሉ በምድርና በሰማይ የእርሱ የሆነውን የጌታ ኢየሱስን ትዕዛዝ እንዴት ማክበር አይገባንም? የማናከብርበትስ ምክንያት ምን ሊሆን ይችላል? “ደቀ መዛሙርት አድርጓቸው” የሚለው ትዕዛዝ ያኔ የተሰጠው ለአስራ አንዱ ደቀ መዛሙርት ነበር። ዛሬ ይህ ትዕዛዝ ለእኛ መሆኑን እናውቃለን? አውቀንስ እየታዘዝን ነው ወይ?

2. *ደቀ መዛሙርት ለማፍራት የጌታ ደቀ መዛሙርት መሆን ያስፈልጋል*። ለአስራ አንዱ ደቀ መዛሙርት ኢየሱስ ቀረበና እንዲህ ተናገራቸው፡- “ደቀ መዛሙርት አድርጓቸው” (ማቴዎስ 28፡ 16-18)። ጌታ “ደቀ መዛሙርት አድርጓቸው” ብሎ ያዘዘው ይከተሉት ለነበሩ ለብዙ ሕዝብ አይደለም። ይህንን ትዕዛዝ የሰጠው ለአስራ አንዱ ደቀ መዛሙርት ነው። እነዚህን አስቀድሞ ጠራቸው፣ ጻልዮም መረጣቸው፤ ጊዜ ወስዶ አስተማራቸውና አሰለጠናቸው። የጌታ ደቀ መዛሙርት ለማፍራት እኛ ራሳችን በእውነት የጌታ ደቀ መዛሙርት መሆን ያስፈልገናል።

በዚህ ዘመን የሚያሳዝነው ግን የጌታ ደቀ መዛሙርት ሳንሆን ለተለያዩ ግለሰቦች ደቀ መዛሙርት መሆናች ን ነው። በእውነት የጌታ ኢየሱስ ደቀ መዛሙርት ብንሆንማ እርስ በርሳችን ጌታ እንደ ወደደን በተዋደድ ን ነበር። በተለያዩ ሰዎች ስም እንደ ቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን ባልተከፋፈልን ነበር (1ኛ ቆሮንቶስ 1፡ 11-13፤ 3፡ 3-
4)። በዘመናችን ብዙ የጌታ ኢየሱስ ደቀ መዛሙርት ሲያፈሩ ማየት ያልተቻለበት ምክንያት ብዙዎቻችን ራሳችን በእውነት የጌታ ደቀ መዛሙርት ባለ መሆናችን ሊሆን ይችላል። ብዙዎቻችን ያለጥርጥር አማኞች ልንሆን እንችላለን፤ ክርስቲያኖችም ልንሆን እንችላለን፤ ግን በእውነት የጌታ ደቀ መዛሙርት ነን ወይ?

ዓለማችን “ክርስቲያኖች ነን”
“የክርስቶስ ደቀ መዛሙርት ነን” በምንል ሰዎች ተሞልታለች። የብዙዎቻችን ሥራና ሁኔታ ግን እውነተኛ ደቀ መዛሙርት አለመሆናችንን እያስመሰከረ ነው። ምክንያቱም በመካከላችን መለያየት፣ ጥላቻና ቅንዓ ት ሞልቶአል። ነገር ግን ዋና ምልክታችን የሆነው ተግባራዊ ፍቅር ጠፍቷል። የጌታ ደቀ መዛሙርት ለማ ፍራት በእውነት የጌታ ደቀ መዛሙርት እንሁን። የጌታ ደቀ መዝሙር የሚያፈራ የጌታ ደቀ መዝሙር የሆ ነ ነው።

3. ደቀ መዛሙርት ለማፍራት ወደ አሕዛብ ሁሉ መሄድ ያስፈልጋል። “ሂዱና አሕዛብን ሁሉ … ደቀ መዛሙርት አድርጓቸው … “ (ማቴዎስ 28፡ 19-
20) ጌታ በሰጠው ትዕዛዝ መሠረት ደቀ መዛሙርት ለማፍራት ደቀ መዝሙር መሆን ብቻ ሳይሆን ወደ አሕዛብ ሁሉ መሄድ ያስፈልጋል። ሰዎች ወደ እኛ እንዲመጡ መጠበቅ ብቻ በቂ አይደለም። የጌታ ደቀ መዛሙርት ወደ አልሆኑ ሰዎች መሄድ ያስፈልጋል። ትዕዛዙ “ሂዱ” ነው። ጌታ ሰዎች ወዳሉበት ሄዶ “ወ ደ እኔ ኑ” ካለ በኋላ ወደ እርሱ የመጡትን አስተማራቸው፣ አሰለጠናቸው፣ ወደ ሌሎች “ሂዱ” አላቸው ። ሰዎችን ወደ ቤተ ክርስቲያን “ኑ” ማለት መጥፎ ባይሆንም ዋናው ትዕዛዝ ግን “ሂዱ” መሆኑን እንገንዘ ብ።

“መሄድ” ሲባል የግድ ሩቅ አገር መሆን የለበትም። ቁም ነገሩ ታዝዞ መሄዱ ላይ ነው። ወደ ጐረቤቶቻች ን ሊሆን ይችላል፤ ወደ ሥፈራችን ሊሆን ይችላል። ጌታ ካዘዘ ደግሞ ወደ ሩቅም ሊሆን ይችላል። ሩቅ የ ሚሄደውም ቅርብ የሚሄደውም ለጌታ ፈቃድ ታዝዞ እስከ ሄደ ድረስ መልካም ይሆናል። ሩቅ የሄደው ቅ ርብ ከሄደው አይበልጥም። አንዳንዶቻችን ወደ ሩቅ አገር የወንጌል አገልግሎት አለ ስንባል የምንሄድ፣ ነገ ር ግን ወደ ሥፈራችን እሑድ ከሰዓት በኋላ ወንጌል ለመስበክ እንሂድ ሲባል ለመሄድ የማንፈቅድ አለን። በሩቅም በቅርብም ያሉ ሰዎች ናቸው። ሁሉም ወንጌል ያስፈልጋቸዋል። ወንጌል ለአሕዛብ ሁሉ ነው። ያ ለ አንዳች አድልዎ ልንሰብክና ሰዎችን የጌታ ኢየሱስ ደቀ መዛሙርት ልናደርግ ይገባናል። ሁላችን የጌታ ደቀ መዛሙርት የሆንነው ወደ አሕዛብም ሁሉ የምንሄደው በመጀመሪያ ስለ ሁሉ በመጸለይ ነው። ወደ አሕዛብ ሁሉ የሚሄዱትን በጸሎትና በመስጠት በመደገፍ እንሄዳለን። ጌታ በከፈተልን በር ደግሞ ራሳችን በመሄድ እንሳተፋለን። ስለዚህ በጸሎት፣ በመስጠትና በመሄድ ሁላችንም ማገልገል ይኖርብናል።

ዛሬ በዓለም ያለነው ሦስት ቢሊዮን የምንሆን ክርስቲያኖች በእውነት የጌታ ደቀ መዛሙርት ብንሆን፣ እያ ንዳንዳችን በዓመት ለአንድ ሰው ብንመሰክርና የጌታ ደቀ መዝሙር ብናደርጋቸው የዓለምን ሕዝብ ሁሉ በወንጌል ለመድረስ የሚፈጀው ከሦስት ዓመት አይበልጥም ነበር። እንግዲህ አለመታዘዛችንና ስንፍናችን ምን ያህል እንደ ሆነ እንመልከት። በዓመት አንድ ሰው ደቀ መዝሙር ማድረግ ነው ያቃተን። ምናልባት ራሳችን እውነተኛ የጌታ ደቀ መዛሙርት መሆን ነው የተሳነን። ጌታ እውነተኛ ደቀ መዛሙርት ያድርገን።

5. ደቀ መዛሙርት ለማፍራት ጌታ ያዘዘውን ሁሉ ማስተማር ያስፈልጋል። “ያዘዝኋችሁንም ሁሉ እንዲ ጠብቁ እያስተማራችኋቸው ደቀ መዛሙርት አድርጓቸው” (ማቴዎስ 18፡ 19-
20) ደቀ መዛሙርት ለማፍራት መሄድ፣ መስበክ፣ ማመን፣ ማጥመቅ ብቻ በቂ አይደለም። አንድ ሰው ወ ንጌልን ሰምቶ ንስሓ ከገባና በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም አምኖ ከተጠመቀ በኋላ ጌታ ያዘዘውን ሁሉ እ ንዲጠብቅ መማር አለበት።

በዘመናችን ወንጌል በመስበክ የተሰማሩ ብዙ ወገኖች አሉ፤ ብዙ አብያተ ክርስቲያናት ዋና ተግባራቸውን ወንጌልን መስበክ ብቻ አድርገዋል። በስብከት የሚያገለግሉ አገልጋዮች አሏቸው። በማስተማር የሚያገለግ

ሉ አስተማሪዎች ግን የሏቸውም፤ ቢኖሯቸውም የታወቀ አይደለም። በሥርዓትና በተያያዘ መልኩ አያስተ ምሩም፤ በተገኘው ቀዳዳ ከስብከት ያልተለየ ትምህርት ብቻ መስጠት ነው የሚችሉ። ጌታ ግን ያዘዝኳች ሁን በከፊል ሳይሆን ሁሉን እንዲያውቁ፣ አውቀው እንዲጠብቁ፣ እንዲታዘዙና ሥራ ላይ እንዲያውሉት አስተምሯቸው  ነው ያለው።

ጌታ ያዘዘውን ሁሉ አውቆ ማስተማር ቀላል አይደለም። መጀመሪያ ራሳችን ተማሪዎች ሆነን በጌታ እግር ሥር ሆነን ጌታ ያዘዘውን መማርና በተግባር ማዋል ይጠበቅብናል። ይህን ስንል ሁላችንም ሥራችንን ትተ ን ወደ መጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤት መግባት አለብን ማለት አይደለም። ጌታ የሰጠንን ሥራችንን እየሠ ራንም ቢሆን ለጌታ ጊዜ መስጠት አለብን ማለት እንጂ።

ሰውን እንዲያውቅ ማስተማር በራሱ ቀላል ተግባር አይደለም። ጌታ ግን ያዘዘን እንዲያውቁ ብቻ ማስተ ማር ሳይሆን አውቀው እንዲታዘዙ አስተምሩ ብሎ ነው። ማወቅ ብቻ በቂ አይደለም ማለት ነው። ሰው አውቆ ሲታዘዝ ነው ደቀ መዝሙር የሚሆነው። አውቆ አለመታዘዝ ከአለማወቅ የባሰ ነው። በዚህ ዘመን በአንዳንድ ሥፍራ መታዘዝ የጐደለው ዕውቀት ሲበዛ፣ በሌላ ሥፍራ ደግሞ ዕውቀት የሌለው መታዘዝ በ ዝቶ ይታያል። ጌታ ያዘዘው ግን ትዕዛዛቱን ሁሉ መሠረት ያደረገ መታዘዝን ነው። የጌታ ደቀ መዛሙርት ለማፍራት ጌታ ያዘዘውን ሁሉ እንዲታዘዙና እንዲጠብቁ ማስተማር ያስፈልጋል።

6. ደቀ መዛሙርት ለማድረግ ስንሰማራ ጌታ ሁልጊዜ ከእኛ ጋር እንደ ሆነ ማወቅ ያስፈልጋል። “እነሆ እኔ እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ ሁልጊዜ ከእናንተ ጋር ነኝ”
(ማቴዎስ 28፡ 20) የጌታ እውነተኛ ደቀ መዝሙር መሆን ቀላል ነገር አይደለም። በእርኩሰት በተሞላች ዓለም፣ ደካማ የሆነ ሥጋ ተሸክሞ የጌታ ኢየሱስ እውነተኛ ደቀ መዝሙር መሆን ከባድ ነው። የጌታ ደቀ መዝሙር ከመሆን አልፎ እውነተኛ የጌታ ደቀ መዛሙርት ማፍራት እጅግ በጣም ከባድ ነው። ታላቅ መ ስዋእትነት ብዙ ፍቅርና ትዕግስት የሚጠይቅ ኃላፊነት ነው። ወንጌል ለአሕዛብ ሁሉ መስበክ፣ በአብ በወ ልድ በመንፈስ ቅዱስ ስም ማጥመቅ ጌታ ያዘዘውን ሁሉ እንዲታዘዙና እንዲጠብቁ ማስተማር ቀላል ኃላ ፊነት አይደለም።

ጌታም የሰጠንን ኃላፊነት ክብደት ስላወቀና በራሳችንም ልንወጣው እንደማንችል ስለ ተገነዘበ እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ ሁልጊዜ ከእናንተ ጋር ነኝ በማለት ታላቅ ተስፋ ሰጥቶናል። ጌታ ሊረዳን፣ ሊመራንና ሊያስችለን ሁልጊዜ ከእኛ ጋር ነው። በእርሱ ታምነን፣ እርሱን ሰምተን፣ እርሱን ታዝዘን የምንወጣና የምንገባ ከሆንን ያዘዘንን ለመፈጸም ያስችለናል። የእርሱ እውነተኛ ደቀ መዛሙርት እንሆናለን። በእውነት የእርሱ ደቀ መዛሙርት የሆኑትን እናፈራለ። በዚህም ትርጉም ያለው ሕይወት ይታይብናል።




ደቀመዝሙር ከምሆን የሚያግደው ምንደነው???

1. መስቀል መሸከም/ መያዝ ያለመፈለግ / ስለ ከርስቶስ የሚደርስን መከራ ለመቀበል ያለመፍቀድ

2. በክርስቶስ መመላለስን ያለመሻት

ሀዋሪያው ጳውሎስ ሁሉም እንደተዉትና ብቻወን እንደቀረ እንደከፉ አድራጊ እስከታሰርና መከራ እስከቀበል ድረስ ደማስ ወደ ተሰሎንቀ፣ ቲቂቆስ ወደ ገላትያ ቲቶ ወደ ደማልጢያ ሲሀዱ ሉቃስ ብቻ አጠገቡ እንደቀረ ይናገራል

- 2ኛ ጢሞ 2፡ 12

ቃሉ የታመነ ነው እንዲህ የሚለው ከእርሱ ጋረ ከሞትን ከርሱ ጋር ደግሞ በህይወት እንኖራለን

ብንጸና ከርሱ ጋር ደግሞ እንነግሳለን

ብንክደው እርሱ ደግሞ ይክደናል

ባናምነው እርሱ የታመነ ሆኖ ይኖራል ራሱን ሊክድ አይችልምና



# ደቀመዝሙር ለመሆን

1. ጸሎት  ዮሀ 15 ፡5 → ያለ ክርስቶስ ምንም ማድረግ ስለማይቻል
2. መማር → ክርስቶስ ያስተምር ነበር

3. መፈጸም → ትዕዛዙን

4. ማካፈል → ህይወታችንን ሳይቀር

ደቀ መዝሙር ማፍራት እንዴት ይቻላል?

- 1ቆሮ 3 ፡__1~5
- 1ተሰ 2፡2

ሀ/ የወላጅ ልብ ባለ ፍቅር

- 1ተሰ2፡7

ለ/ አብሮ መህድ

ክርስቶስ → ከደቀመዝሙሩ ጋር

ጳውሎስ → ከጢሞቲዎስ ና ቲቶ ጋር

**1. ጸሎት የሀ 15 ፡5**

ማት 6፡ 9. እንግዲህ እናንተስ እንዲህ ጸልዩ_______

**ጸሎት**

- ✓ ፍቃዱን እንድናውቅ ያደርገናል
- ✓ ከክፉ እንድንጠበቅ ይረዳናል
- ✓ መንፈሳዊ ጥንካረ ይሰጠናል

- የሀዋርያቶች መታወቂያ ትምህርትና ጸሎት ነው ሀዋ 4
- ጴጥሮስን ከእስር ያስፈታው ጸሎት ነው ሀዋ 12
- በመከራ ወቅት ብርታትን የሚሰጠው ጸሎት ነው

**መማር**

**የማቴዎስ ወንጌል 7፡24፤ ስለዚህ ይህን ቃሌን ሰምቶ የሚያደርገው ሁሉ ቤቱን በዓለት ላይ የሠራ ልባም ሰውን ይመስላል።**

**የማቴዎስ ወንጌል 7፡28፤ ኢየሱስም ይህን ነገር በጨረሰ ጊዜ ሕዝቡ በትምህርቱ ተገረሙ፤**

**የማቴዎስ ወንጌል 13፤ በምሳሌም ብዙ ነገራቸው፥ እንዲህም አላቸው፦ እነሆ፥ ዘሪ ሊዘራ ወጣ።**

**የማቴዎስ ወንጌል 13 ፡ 10፤ ደቀ መዛሙርቱም ቀርበው፦ ስለ ምን በምሳሌ ትነግራቸዋለህ? አሉት።**

**የማቴዎስ ወንጌል 13፡11፤ እርሱም መልሶ እንዲህ አላቸው፦ ለእናንተ የመንግሥተ ሰማያትን ምሥጢር ማወቅ ተሰጥቶአችኋል፥ ለእነርሱ ግን አልተሰጣቸውም።**

**በምሳለ ክርስቶስ ያስተምር ነበር**

**ስለ መንግስተሰማይ በማቲዎስ 13፡ ላይ በምሳለ አስተማራቸው**

- **ስለ እንክርዳዱ**
- **ስለ ሰናፍጭ ዘር**
- **የእርሾው ምሳለ**

- **የዘሪው ምሳለ**
- **በት በአሸዋና በአለት ላይ የሰራ ሰው ምሳለ**

**ሉቃስ 15፡1**

**ጠፍቶ የተገኘው ምሳለ**

- ✓ **ጠፍቶ የተገኘው በግ**
- ✓ **ጠፍቶ የተገኘው ብር**
- ✓ **ጠፍቶ የተገኘው ልጅ በየጠፋው ዲናር ምሳለ**
- ✓ **የጠፋው ልጅ ምሳለ**

**አደራ ለአገልጋዮች የሰጠው ሀብታም ሰው ምሳለ ሉቃስ 11፡11**

*መፈጸም ትዕዛዙን*

*ኦሪት ዘዳግም 6፡ 24፤ እንደ ዛሬም በሕይወት እንዲያኖረን፥ ሁልጊዜም መልካም እንዲሆንልን፥ አምላካችንን እግዚአብሔርን እንፈራ ዘንድ፥ ይህችንም ሥርዓት ሁሉ እናደርግ ዘንድ እግዚአብሔር አዘዘን።*

*ኦሪት ዘዳግም 10፡12-13፤*

*እስራኤል ሆይ፥ አሁንስ አምላክህን እግዚአብሔርን ትፈራ ዘንድ፥ በመንገዱም ሁሉ ትሄድ ዘንድ፥ አምላክህንም እግዚአብሔርን ትወድድ ዘንድ፥ በፍጹምም ልብህ በፍጹምም ነፍስህ ታመልከው ዘንድ፥ መልካምም እንዲሆንልህ ዛሬ ለአንተ የማዝዘውን የእግዚአብሔርን ትእዛዝና ሥርዓት ትጠብቅ ዘንድ ነው እንጂ አምላክህ እግዚአብሔር ከአንተ የሚፈልገው ምንድር ነው?*

የሉቃስ ወንጌል 10፡25፤ እነሆም፥ አንድ ሕግ አዋቂ ሊፈትነው ተነሥቶ፡- መምህር ሆይ፥ የዘላለምን ሕይወት እንድወርስ ምን ላድርግ?

26፤ እርሱም፡- በሕግ የተጻፈው ምንድር ነው? እንዴትስ ታነባለህ? አለው። የሉቃስ ወንጌል 10

27፤ እርሱም መልሶ፡- ጌታ አምላክህን በፍጹም ልብህ በፍጹም ነፍስህም በፍጹም ኃይልህም በፍጹም አሳብህም ውደድ፥ ባልንጀራህንም እንደ ራስህ ውደድ፡ አለው። የሉቃስ ወንጌል 10

28፤ ኢየሱስም፡- እውነት መለስህ፤ ይህን አድርግ በሕይወትም ትኖራለህ፡ አለው።

እግዚአብሀርን በፍጹም ልብህ ሀይልህ ነፍስህ ውደድ

ባልንጀራህን እንደራስህ ውደድ

ማካፈል

ተሰ 2

2ቆሮ8፡ 1